# የተማሪዎች ህብረት ምርጫ መመሪያ

**ለአስመራጭ ኮሚቴ ኦሬንቴሽን የቀረበ ገለፃ**

**ሕዳር 2011 ዓ.ም**

# መግቢያ

- በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ፤ የልማትና የሰላም ስትራተጂዎችና ፕሮግራሞች እንቅስቃሴ በመሳተፍ ለውጥ ለማምጣት፤ የአገር ተቆርቋሪነትና የአንድነት ስሜት ለማዳበር፤ የሀገራችን የረጅም ዘመን አብሮና ተቻችሎ የመኖር ባህል በበለጠ ለማጠናከር፤ለፈጣን ዕድገት አዎንታዊ ሁኔታዎችን በመፍጠር ረገድ እኛ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ከፍተኛ ድርሻና የማይተካ ሚና እንዳለን ስለምናምን፤

- የሃገራችን ጉዳይ ስለሚመለከተን፤ሃገራችንና ህዝባችን ካሉበት አዝጋሚ የኢኮኖሚ ጉዞ ወጥተው ሌሎች ከደረሱበት ዘርፈ ብዙ እድገት ደረጃ እንዲደርሱ ከሚያግዙት ዋና ዋና እድገት መሸጋገሪያ ድልድዮች አንዱና ተቀዳሚ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በህብረት ሃይላችንን አጠናክረን ከፊታችን የተደቀነውን ድህነት ተፋልመን የምንፈታበትና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት እንዲሁም የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ሆነን የምንሰራበት ሁኔታ ለማመቻቸት ጠንካራ ህብረት መመስረት አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘነው የተማሪዎች ህብረት የተማሪዎች አደረጃጀት መመሪያና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በአባላት ሙሉ ፈቃድ ተመስርቷል፡፡

# የቀጠለ ...

- የኢትዮጲያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ህብረት በሀገሪቷ ውስጥ ባሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ህብረት አማካኝነት የተቋቋመ ሲሆን ዋና አላማውም በአባልነት ያሉ የህብረቱ አባል ህብረቶችን ሁለንተናዊ ጉዳዮች ለማስፈጸም ብሎም በተናጠል ሳይሆን በጋራ በመሆን ለችግሮቻችን መፍትሄዎችን እያበጀን እንድንሄድ ሳሉን መልካም ተሞክሮዎች ደግሞ ለሌሎች እያካፈልን ጠንካራና የተማረውን አካዳሚክና አገልግሎት ነክ ጉዳዮች ዙሪያ **ተማሪዎችን በመወከል** ጥያቄዎችን ማቅረብ ብሎም በተቋሙ አመራሮች እና በተማሪው **መካከል ድልድዩ** በመሆን ለማገዝ የሚረዳ መሆኑ ይታወቃል::

# የቀጠለ ....

- ስለሆነም ህብረቱ እንደሌሎች ህብረቶች የራሱን የሆነ የአባል ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ህብረት
  - አሠራረጥ ወጥ ማድረግና በተማሪና ተማሪ ብቻ የተሠረጠ በዘር፣ በሀይማኖት፣ በብሄር እና በሌሎች ጉዳዮች ታሳቢ ተደርጎ ያልተሠረጠ፣
  - ይልቁንስ ለሠረጠው ተማሪ፣ ለሚማርበት ተቋም፣ ለሀገር ተቆርቋሪና ፍትሀዊ የሆነ አገልግሎት ሰጪ የተማሪዎች ህብረት አሠራሮችን ማምጣት አስፈልጓል።

# የቀጠለ

- በመሆኑም ይህ መመሪያ ሲዘጋጅ ከዚህ በፊት በነበረው በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የምርጫ ስርዓት ብሎም ህብረቱ በተለያዩ አካላት በሚካሄድበት **ጣልቃ ገብነት** ምክንያት በተማሪዎች መሰራት የነበሩባቸው ስራዎች ሳይሰሩ ቀርተው ተማሪዎች ጥያቄዎቻቸው ሳይጠየቅ በመቅረቱ ብቻ እና የራሳቸውን ተወካዮች አግኝተው ባለማወቃቸው ባንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች የተለያዩ ችግሮች ሲያጋጥሙ ቆይተዋል

- ከዚህም አልፎ በሚፈጠሩ ቀውሶች ውስጥ **እጃቸው ሲኖርበትም** ተስተውሎአል፡፡

- ስለሆነም ይህ መመሪያ **በስራቸው ምርጥና ከጣልቃ ገብነት የጸዱ ለተማሪዎች ብሎም ለተቋም በእኩል አይን በማየት አመዛዝነው ሲመሩ** ከነበሩ የተማሪዎች ህብረት ልምዶች ተወስደው የተቀረጹበት ሲሆን ከዚህም ባለፈ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተስተዋሉትንም ክፍተቶች ለመሙላት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

- **ክፍል አንድ**

- **አንቀጽ አንድ**

- **የመመሪያው አስፈላጊነት**

  - የዚህ መመሪያ አስፈላጊነት በኢትዮጲያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ የተማሪዎች ህብረት ሳይ ወጥ የሆነ የምርጫ ስርዓት እንዲኖር በማድረግ ግልጽነት ተጠያቂነት የተላበሰ ትክክለኛ እና ብቃት ያለው ከዘር፤ ከሀይማት፤ ከብሄርና ሌሎች ድርጊቶች ያስተካፈሉበት ነጻና ፍትሀዊ የሆነ የምርጫ ስርዓት እንዲኖር ለማድረግና በተማሪዎች ለተማሪዎች የተመረጠ የተማሪዎች ህብረት አመራር ለማዋቀር ተዘጋጀ ነው።

- አንቀጽ ሁለት

- ዓላማ

- 
  - የዚህ የተማሪዎች ህብረት የምርጫ ስርዓት ዋና ዓላማ በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች እየተስተዋሉ ያሉ በተማሪዎች ህብረት ዙሪያ የሚፈጠሩ ክፍተቶችን ብሎም ተማሪዎች ጥያቄዎቻቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዳይጠይቁ የሚያደርጉና የወከላቸውን ተማሪ ከመዘንጋት አልፈው ተማሪዎች ብሎም ሀገር የጣለችባቸውን አደራ ሳይወጡ በመቅረት ለሰማዊ መማር ማስተማሩን የሚያደፈርሱ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። በመሆኑም የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ እነዚህን ችግሮች በመፍታትና በግልጽ በተማሪዎች ቀጥተኛ ውክልና የተመረጡ ብሎም በተማሪውና በዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት መካከል ድልድይ ሆነው የሚያገለግሉ የተማሪዎች ህብረት አመራሮችን ማስመረጥና በሁሉም ዩኒቨርሲቲ ወጥ የሆነ ሁሉም ተማሪዎችን የሚወክል ሰላምን፣ አንድነትን፣ መቻቻልን፣ አብሮ መኖርን የሚያስተምሩ ካሉበት ዩኒቨርሲቲ አልፈው ለማህበረሰቡ ጠቃሚ የሆነ ለሀገር ደግሞ መልካም ለምዶችን ቀምረው በመውጣት ለነገ የዚህች ሀገር የነገ ተረካቢ የሆኑ አመራሮችን ማፍራት ጭምር ነው።

- አንቀጽ ሶስት
- አጭር ርእስ
- ይህ የምርጫ እና የአስመራጭ ኮሚቴ የተማሪዎች ህብረት የምርጫ አፈጻፀም መመሪያ ቁጥር--------/2011 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

- **አንቀጽ አራት**
- **ትርጓሜ**

**4.1"መተዳደሪያ ደንብ"** ማለት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ህብረት መተዳደሪያ ደንብ ነው፤

**4.2"ጠቅላላ ጉባኤ"** ማለት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ህብረት ጠቅላላ ጉባኤ ነው::

**4.3"ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች"** ማለት በጠቅላላ ጉባኤ ቀጥተኛ ምርጫ የተመረጡ የህብረቱን የዕለት ተዕለት ሥራ የሚያከናውኑፕሬዚዳንት፤ ም/ፕሬዚዳንትና ፀሃፊ ማለት ነው፤

**4.4"የሥራ አስፈፃሚ(ዘርፍ)"** ማለት በጠቅላላ ጉባኤው የሚተደቀ ሲሆን በዋና ሥራ አስፈፃሚዎች አቅራቢነት እና ተጠሪ ሆነው የህብረቱ ዘርፎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በበላይነት የሚመራ ሲሆን፤ የሴቶች ጉዳይ እና አካል ጉዳተኛ ተጠሪ በራሳቸው አደረጃጀት በኩል ተመርጠው የሚመጡ ይሆናሉ::

**4.5"የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች"** ማለት በዩኒቨርስቲ በመደበኛ የትምህርት ፕሮግራም የሚማሩት ተማሪዎች ናቸው::

**4.6"ህብረት ወይም ህብረቱ"** ማለት እንደ አግባብነት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ህብረት ነው::

**4.7"ነኡሳን ኮሚቴ"ማለት** የህብረቱን ሥራ ለማከናውን እንደ አስፈላጊነቱ የሚቋቋምና በየዘርፉ አመራሮች ወይም ሥራ አስፈፃሚዎች የሚመሩ የተለያዩ ዘርፎች አባላት የያዘ ሲሆኑ የም/ቤቱ አባላት የሆኑና በፍላጎት ዘርፍ የተመረጡ እንዲሁም የየዘርፉን የዕለት ተዕለት ሥራ የሚያከናውኑ ናቸው::

**4.8"ኢጀንሲ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 621/2001 የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ህብረት ኢጀንሲ ነው::

- አንቀጽ አምስት
- የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን

.

- ይህ መመሪያ በኢትዮጲያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስር በሚገኙ ተጠሪነታቸው ለዋናው የኢትዮጲያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ህብረት ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፣

## • ስለ ህብረቱ መዋቅር

1. ህብረቱ ሁሉም አባላት በተወከሉበት የጠቅላላ ጉባኤ ይመራል፤
2. ጠቅላላ ጉባኤው ከእያንዳንዱ **የትምህርት ክፍል ሁለት አባል ይዋቀራል**፤
3. ህብረቱ በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየሙ የዋና የሥራ አስፈፃሚ፤የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ እና ሌሎች አስፈላጊ ኮሚቴዎች ወይም ሥራ አስፈፃሚዎች ይኖሩታል፡፡
4. ጉባኤው ምርጫ ሲያደርግ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ 7-11 አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡
5. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ **የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወሰኑ** አድርጎ ምርጫውን ያስፈፅማል፡፡
6. የምርጫ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ተመራጮች በድጋሚ እንዲያገለግሉ ከተፈለገ በጥቅማ ለውድድር ቀርበው በድምጽ ብልጫ መመረጥ ይኖርባቸዋል፡፡
7. የአባላት ቁጥር ከመብዛቱ የተነሳ የማህበሩን አባላት በሙሉ መሰብሰብ ካልተቻለ **በውክልና መሰብሰብ ይቻላል፡፡** ውክልናው እንደ አስፈላጊነቱ በካምፓስ፤ በኮሌጅ ወይም በትምህርት ክፍል ይሆናል፡፡ የአወካከሉ ሰርዓት በህብረቱ ውስጠ ደንብ ይወሰናል፡፡
8. ለጉባኤው ከተወከሉ የህብረቱ ወይም የህብረቱ ም/ቤት አባላት መካከል **ከግማሽ በላይ** ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤው ይሆናል፡፡
9. የጉባኤው ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው በተገኙ አባላት **ከግማሽ በላይ ድምጽ** ይሆናል፡፡ ድምጽ እኩል ሲሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

- ምዕራፍ ሁለት
- አንቀጽ አንድ

## 1.1 የምርጫ ቦርድ ወይም ምርጫ ኮሚቴ ስለማቋቋም

– በዚህ ርእስ ስር ነባር ዩኒቨርሲቲ ከሆነ የሚከተሉትን ተግባርት የሚያከናዉኑ ይሆናል፡፡በዚሁ መሰረት የምርጫ ኮሚቴዉ ብዛት እና አወቃቀር ከዚህ በታች እንደተጠቀሰው ይሆናል፡፡

1.ብዛት፡- ከ 7 እስከ 11 (ከሰባት እስከ አስራ አንድ) ሊሆኑ ይችላል፡፡

# የቀጠለ....

## 1.2 የምርጫ ቦርድ አባላት አሰያየም እና ዝርዝር አባላት

1. ከተማሪዎች ህብረት ሴቶች ጉዳይ 1
2. ከቀድሞ ህብረት አመራሮች (ቢያንስ 3)
3. ከጋርሳው (በእጅ ወይም በጥቆማ ሊደረግ ይችላል) (ቢያንስ 3)
4. የቀድሞ ህብረት ከአስመራጭ ኮሚቴ ውጭ መሆን የለበትም
5. የምርጫ ሂደቱ ጋርሳሜንተሪ ሲስተም ቢሆን ይመረጣል

6.1(ኘሬዚደንሻል ስመሆን ቢፈለግ ሁሉንም የምርጫ መስፈርት አሟልቶ የመጨረሻውን የምርጫ ስነስርአት ብቻ ለዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች እንዲቀርብ ይደረጋል)

- እንቀጽ ሁለት

## 1.3 ጠቅላላ ጉባኤ ወይም ፓርላማ አወቃቀር

- ጠቅላላ ጉባኤው ወይም የፓርላማው ብዛት በተቋሙ ውስጥ እንደሚገኘው የመማሪያ ክፍል የሚወሰን ሲሆን ይህም ከያንዳንዱ ክፍል ባሉ በሚመረጡ የክፍል መደበኛ ሴትና ወንድ ተወካዮች አማካኝነት የሚመረጡ አባል ይሆናሉ፡፡(ለተማሪዎች ህብረት ተብሎ ለብቻ መምረጥ አይቻልም)፡፡

- አንቀጽ ሶስት

## 3.1 የክፍል ተወካዮች አመራረጥ

- የትምህርት ክፍል ሀላፊ ከተማሪዎች ህብረት ጋር በዋና ስራ አስፈጻሚ መሪነት በመሆን የክፍል ተወካይ በሁሉም በትምህርት ክፍሉ ውስጥ የሚገኙ ክፍሎት ላይ የወንድ እና ሴት ተወካዮችን ያስመርጣሉ፡፡

# የሚመረጡ ተመራጮችም የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1. ጥሩ ስነ-ምግባር ያላቸውና በተማሪዎች የሚታመንባቸው(ይህ ማለት በየትኛውም የዲስፕሊን ቅጣት ያላገኘ)፣
2. የክፍሉን ተማሪዎች ጥቅም ማስጠበቅ የሚችሉ፣
3. ከእምነት፣ ብሄር እና ፖለቲካ፤ ገለልተኝነት የጸዳ/ች፣
4. በሁሉም የዩኒቨርሲቲው እና ህብረቱ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ ያለበት፣
5. ኃላፊነታቸውን እና ግዴታቸውን በአግባቡ የሚወጡ፣
6. ህብረቱ በሚሰጣቸው ስራዎች እና መመሪያዎች መስራት የሚችል፣
7. የአካዳሚክ ውጤት እንደስፈላጊነቱ

# አንቀጽ አራት

## 4.1 የእጩ ተመራጭ ተማሪዎች አመራረጥ

የመጀመሪያው አስመራጭ ኮሚቴው ለፓርላማው በእጅ ጥቆማ እና በፍላጎት ይመዘግባል መስፈርቶቹ፡-

- በዚህ መስፈርት እንደ ዩኒቨርሲቲው ነባራዊ ሁኔታ እስከ 5 ነጥብ ይይዛል
  1. በትምህርቱ ያለው ውጤት(መነሻ 2.75 ሆኖ እንደ ዩኒቨርሲቲው ሁኔታ እስከ 3.2 ድረስ ሊሄድ ይችላል) ከዚህ በታች ከሆነ ምርጫ ውስጥ አይገባም፡፡
  2. በስነ ምግባር ሞዴል የሆነና መሆን የሚችል(ይህ ማለት በየትኛውም የዲስፕሊን ቅጣት ያላገኘ) የዲስፕሊን ቅጣት ከሆነ ምርጫ ውስጥ አይገባም፡፡
  3. የተማሪውን ጥቅም ከዩኒቨርሲቲው እና ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማመዛዘን ማስጠበቅ የሚችል፡፡
  4. ከዚህ በፊት በክበባትና በተለየዩ አደረጃጀት የተሳተፈበት ሰርተፍኬት ማቅረብ የሚችል፡፡ በተለይ በተማሪዎች ህብረት ያገለገለና የሁለት አመት እድሜ ያለው፡፡(ከሴለው ነጥብ አይሰጠውም እንጂ ከውድድሩ አይወገድም)

• **አንቀጽ አምስት**

## 5.1 ለዋና ስራ አስፈጻሚ የሚወጣ ተማሪዎችን ስለመለየት

- አስመራጭ ኮሚቴው ተማሪዎቹን ለዩት **ለዋና ስራ አስፈጻሚነት** (ፕሬዘዳንት፣ ም/ፕረዘዳንት እና ዋና ጸሀፊ) መወዳደር የሚፈልጉ ተማሪዎችን ለፓርላማ ለማቅረብ የጽሁፍ እና የኢንተርቪው ፈተናዎች ያዘጋጃል፡፡

• **የፈተናው አካሄድ.....**

- **የጽሁፍ ፈተና ከ10 ይሆናል**
- ፈተናው በምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው አማካኝነት የሚዘጋጅ ሲሆን የፈተናዎቹ ይዘት እንደየ ዩኒቨርሲቲው ነባራዊ ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል፡፡
- የሚወጡት ፈተናዎች ሚስጥራዊና ለተወዳዳሪ ተማሪ በፍጹም መውጣት የሌለበትም ይህ ሆኖ ከተገኘ እና ኮሚቴው ተወያይቶ ካመነበት ፈተናው ውድቅ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ፈተናው የሚዘጋጀው ከፈተናው 1 ሠዓት በፊት መሆን አለበት፡፡
- አስመራጭ ኮሚቴው ፈተና በሚፈትን ጊዜ **የዩኒቨርሲቲው ተወካይ ሙሉ ሂደቱን የመከታተል መብት ይኖረዋል፡፡** ክፍተት እንዳለ ሲታመን ከፍተኛ የዩኒቨርሲቲው አመራር ለትምህርት ሚኒስቴር ሪፖርት በማድረግ ትምህርት ሚኒስቴር ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ህብረት ጋር በመሆን ሁኔታው ይፈታል፡፡

## • የኢንተርኔት አላማ...

- አስመራጭ ኮሚቴው ኢንተርኔቱ ከ10 ፐርሰንት ይይዛል
- የኢንተርኔቱ ጥያቄዎች በኮሚቴው የሚዘጋጁ ሲሆን ለያንዳንዱ ጥያቄዎች ተወዳዳሪዎች መልስ የሚሰጡ ይሆናል፡፡ በመልሳቸው መሰረት ሙሉ ኮሚቴው በድምር ለተወዳዳሪው የሰጠው ለኢንተርኔቱ ያመጣው ውጤት ይመዘገባል፡፡

- ስራ ዶክመንቶችን ስለማቅረብ...

- አስመራጭ ኮሚቴው እስከ 15 ፐርሰንት ይይዛል
- ስትራቴጂክ ፕላን እና የአሰራር ሂደት በሶፍት ኮፒ እና በሀርድ ኮፒ ለአስመራጭ ኮሚቴው በተሰጠው ጊዜ ማቅረብ ይኖርበታል፣ ኮሚቴው ከሚያስቀምጠው የጊዜና ሰዓት ዘግይቶ የሚያቀርብ ተቀባይነት አይኖረውም ውድቅም ይሆናል፡፡(ከባድ የሆነ የማህበራዊ ችግር መሆኑ ከታመነ ሊቀበል ያስችላል፡፡)

- **አንቀጽ ስድስት**

## 6.1 የአመራረጥ ስነ-ስርአት

1. ያስገቡትን የመወዳደሪያ ፕሮፖዛል ለፓርሳማው ተወዳዳሪዎች እንዲያቀርቡ እኩል ሰዓት ሰጥቶ ማስቀረብ:: ሲቀርብም ከዘረኝነት፣ ከብሄር፣ ከእምነት፣ እና ሌሎች አሳስፈሳጊ ቅስቀሳዎችን የተቆጠበ መሆን አለበት::
2. የፓርሳማ አባላት ጥያቄዎቻቸውን እዛው መድረክ ላይ ተማሪዎቹን እንዲጠይቁ ማድረግ ስዚህም ተመራጮች ምላሽ እንዲሰጡ እድሉን መስጠት::
3. ከላይ በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሰው እንደተጠናቀቀ ለፓርሳማው የተመራጮች ፎቶ የያዘ ወረቀት በመስጠት እንዲመረጡ ያደርጋል ::ተመራጮቹ ሂደቱ ፍትሀዊ እንዲሆን ታዛቢ የማስቃወም መብት አላቸው ::
4. ምርጫው በእጅ ብልጫ ወይም በጥቆማ ሲሆን ስለማይችል የምርጫ ኮሮጆ ተዘጋጅቶ እንዲመርጡ ይደረጋል አብላጫ ቁጥር ያገኘ ተማሪ የህብረቱ ፕሬዘዳት ም/ፕሬዘዳት እና ዋና ጸሀፊ በመባል የመረጣል::
5. የህብረቱ ዋና ዐዲተር ከፓርሳማው ለብቻው የሚመረጥ በዚሁ ቀን በጉባኤው የሚመረጥ ይሆናል ::
6. ሀይብሪድ የምርጫ ስርአትን የሚከተል ዩኒቨርሲቲ ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርትና ሂደት ከሄደ በኋላ ስትራቴጂክ እቅዱን ሰና የስራ ሂደቱን ከዘረኝነት፣ከብሄር፣ ከእምነት፣ እና ሌሎች አሳስፈሳጊ ቅስቀሳዎችን የተቆጠበ በማድረግ ለግቢው ተማሪ እንዲቀርብ ይደረጋል::አብላጫ ቁጥር ያገኘ ተማሪ የህብረቱ ፕሬዘዳት ም/ፕሬዘዳት እና ዋና ጸሀፊ በመባል የመረጣል::

7. አስመራጭ ኮሚቴው፣ እጩ ተወዳዳሪ ወይም ዩኒቨርሲቲው በምርጫ ሂደቱ ላይ አሳስፈሳጊ የምርጫ ቅስቀሳ ሲደረግ በማስረጃ ከያዘ እጪ ተወዳዳሪውን ሙሉ በሙሉ የማሰናበት ወይም እንደ ጥፋቱ መጠን ውጤት ሲቀንስ ይችላል::

• አንቀጽ ሰባት

## 6.2 የተመረጭ የህብረቱ ከፍተኛ አመራር ተግባር

1. የስራ አስፈጻሚ ምርጫ የሚሆነው ለዋና ስራ እስፈጻሚ ተወዳድረው ከሶስቱ ውጭ የሆኑትን በመመልመል ከስራቸው የሚመረ ዝቅተኛ 12 (አስራ ሁለት)-14(አስራ አራት) ስራ አስፈጻሚዎችን ይሾማሉ በመቀጠልም ለፓርላው አቅርበው ያፀድቃሉ ፡፡
2. የሴቶች እና አካል ጉዳተኛ ተጠሪ ለብቻቸው የሴቶች ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ሁሉም ሴቶች የሚመርጧት የሴት ተማሪዎች ኘሬዘዳንት የተማሪዎች ህብረት የሴቶች ጉዳይ ትሆናለች፡፡ የሴቶችን ጠቅላላ ጉባኤ በተማሪዎች ህብረት አስተባባሪነት የሚካሄድ ሲሆን ሙሉ የምርጫ ስርአቱ ከላይ የተዘረዘረውን እንደመነሻ ተደርጎ የሚሄድ ይሆናል፡፡
3. የአካል ጉዳተኛ ተጠሪም ወይም አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ሰብሳቢ የተ/ህብረት አካል ጉዳተኛ ዘርፍ ሰብሳቢ ይሆናል ይህም ተማሪዎቹ ተሰብስበው የሚመርጡት ተማሪዎች ህብረት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተወካይ ይሆናል፡፡
4. የዚህ ምርጫ አሸናፊዎች ይህ ምርጫ በተካሄደ ባሉት ሁለት አመታት የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ህብረት ሆነው ሚቆዩ ይሆናል፡፡
5. የተሸሙት ዘርፍ አመራሮች በስራቸው ሚሰሩ አባላትን፣ ንኡሳን ኮሚቴዎችን እና አጋዥ አካላትን የመመልመል መብት ይኖራቸዋል፡፡

- <u>ምእራፍ ሶስት</u>
- <u>የአባላት መብትና ግዴታ</u>

- <u>አንቀጽ  አንድ</u>

- <u>የአባላት መብት</u>

1. ሁሉም አባል እኩል መብት አላቸው፤
2. የመምረጥ፤የመመረጥና የህብረቱን እንቅስቃሴ አስመልክቶ ማንኛውንም መረጃ የማወቅ፤
3. በህብረቱ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በቀጥታ ወይም በውክልና የመገኘት፤ስለህብረቱ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት፤
4. በህብረቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ ድምጽ የሚኖረው ሲሆን የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱም በህብረቱ ውስጠ ደንብ ይወሰናል፡፡

- **<u>አንቀጽ ሁለት</u>**
- **<u>የአባላት ግዴታ</u>**

1. የአባልነት መዋጮ በወቅቱ የመክፈል፤
2. የህብረቱን መተዳደሪያ ደንብ፤ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡ መመሪያዎችና ውሳኔዎችን የማክበር፤
3. የህብረቱን አላማ የማክበርና በተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ እንዲያገለግል ሲመረጥ የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት፤
4. በህብረቱ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት፤
5. ትምህርቱን ሲጨርስ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ትምህርቱን ሲያቋርጥ ከህብረቱ የተሰጠውን መታወቂያና ለስራ የተረከበውን ንብረት የመመለስ ግዴታ እና፣
6. በህብረቱ ውስጥ ከአንድ የኃላፊነት ቦታ ወደ ሌላ የኃላፊነት ቦታ ሲሸጋገርና ከተለያዩ የሃላፊነት ደረጃዎች ሲወርድ በእጁ የነበሩ ንብረቶችን ለህብረቱ የማስረከብ፤

- **<u>አንቀጽ አስራ ሦስት</u>**
- **<u>አባልነት የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች</u>**
- አንድ የህብረቱ አባል አባልነቱ ሊቋረጥ የሚችለው፡-

1. ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ
2. ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የህብረቱ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲሰናበት ሲወሰን፡፡
3. በራሱ ፍቃድ ሲወሰንና ሲጠይቅ፤
4. የህብረቱ ክብርና ህልውና በሚነካ ወይም በሚያናጋ ተግባር ላይ መሳተፉ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፤
5. ከዩኒቨርሲቲው በማናቸውም ምክንያት ሲሰናበት ወይም ሲያቋርጥ፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (5) የተጠቀሱት እንደተጠበቀ ሆኖ የህብረቱ ጠቅላላ ጉባኤ በሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ አባል ከአባልነቱ እንዲታገድ ማድረግ ይችላል፤

ሀ/ በዩኒቨርስቲው በተማሪዎች የስነምግባር መተዳደሪያ ደንብ (Code of conduct) ከአንድ ዓመት በላይ በሚያስቀጡ ጥፋቶች ላይ ተሳታፊ ሲሆን፤
ለ/ ከተማሪዎች ህብረት አባላት የማይጠበቅ ማንኛውም ድርጊት ፈጽሞ ሲገኝ፤
ሐ/ በህብረቱ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተጣለበትን ግዴታ ሳይወጣ ሲቀር፤
መ/ ጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጠውን ምክር እና ተግሳጽ ባለማክበር ተደጋጋሚ ጥፋት ሲያጠፋ እና
ሠ/ ጠቅላላ ጉባኤው በሌላ አጥጋቢ ምክንያት ከአባልነት ሲያሰናብተው

ረ/ ዝርዝር መስፈርቱ በጠቅላላ ጉባኤው የሚወሰን ሆኖ ስብሰባዎችን ስተወሰኑ ጊዜያት የቀረና በጉባኤው ስተወሰነው ጊዜ ያክል ከዘርፍ /ንዑሳን/ ኮሚቴዎች ውስጥ ቢያንስ በአንድ አስመንቀሳቀሰ፤

**ህብረቱ በሚከተለው መልኩ የተዋቀረ ነው።**




የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆነ ማንኛውም ሰው በተጨማሪ ኦዲተር ሆኖ ሊሰራ አይችልም።

- **የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር**

## የህብረት ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ጠቅላላ ጉባኤው የህብረቱ የበላይ አካል ነው፤
2. የሥራ አፈፃፀም ኮሚቴ አባላትንና የኦዲት ኮሚቴን ይመርጣል፤ይሸራል፤
3. በህብረቱ የሥራ ፕሮግራምና ስትራተጂ አቀጣጫ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤
4. ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም በመመርመር ለቅድና በጀት ያፀድቃል
5. ዓመታዊ የሥራና የኦዲት ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፤
6. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚያቀርበውን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በማዳመጥ ህብረቱ የተቋቋመበትን ዓላማና የተነደፉ መርሃ ግብሮች ተግባራዊ መሆን አለመሆናቸውን ያረጋግጣል፤
7. የህብረቱን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፤ያሻሽላል፤
8. የህብረቱ ሂሳብ በኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የውጭ ኦዲተርም ይሰይማል፤

# የቀጠለ….

9. በህብረቱ መፍረስ እና ንብረት ማጣራት ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤
10. ስሌላ የህብረቱ አመራር አካል ያልተሰጡ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤
11. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11 በተገለፀው መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከአባልነት እንዲረዝ ይወስናል፤
12. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ያወጣል፤
13. ህብረቱ ከሌሎች ህብረቶችና ማህበራት ጋር ማህበር ለመፍጠር ወይም ለማዋሃድ ወይም የመካፈል ወይም መለወጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤
14. በህብቱ ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ ህብረቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤
15. ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህግጋት ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መተዳደርያ ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።
16. የህብረቱን ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት አማካሪ ያፀድቃል ይሾራል።

## • <u>የኦዲትና ቁጥጥር ዘርፍ</u>

1. የህብረቱ ኦዲት የህብረቱ ፕሬዚዳንት ወይም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ሊሆን አይችልም፤
2. የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

   ሀ/ የህብረቱ ገንዘብና ንብረት አስተዳደር ይቆጣጠራል፤

   ለ/ የህብረቱ የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪ ደንብ መሰት መካሄዱን ያረጋግጣል፤

   ሐ/ ዓታዊ የኦዲት ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀባል፤
3. በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡትን ተመሳሳይ ተግባርና ሃላፊነት ያከናውናል፤

# መዋቅር


ጠቅላላ ጉባኤ
ዋና ኦዲት
የውስጥ ኦዲት
ክንውን ኦዲት
የንብረት ኦዲት
የፋይናንስ ኦዲት
የቢሮ እቃዎች
በጎ አድራጎት እና ክበባት
የምግብ እና ተያያዥ ነገሮች
የተማሪ አገልግሎት
ደጋፊ
አካዳሚክ

- **የቀድሞው ህብረት** ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ህብረት እና ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር አዲሱ አመራር ከተመረጠ በኋላ ጠቅላላ ስልጠና እና ኦሬንቴሽን የመስጠት ግዴታ ይኖርበታል፡

- **የስልጣን ሽግግሩ** ለተማሪዎች ግልጽ በሆነ መንገድ በማስታወቂያ፣ በማህበራዊ ድህረ-ገጽ እና በተለያየ መንገድ ሊተዋወቅ ይገባል፡፡

- **የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራር** አዲስ የተመረጡትን አመራሮች መድረክ በመፍጠር ወይም በተፈጠረ መድረክ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ማስተዋወቅ እና አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲደረግላቸው የማድረግ ሀላፊነት ይኖርባቸዋል፡ለትምህርት ሚኒስቴር፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ህብረት፣ ለትምህርት ክፍል ፣ ኮሌጆች፣ በተለያዩ ዳይሬክተር ቢሮዎች፣ ለዞን፣ ለክክልል እና እንዳስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በደብዳቤ ማንነታቸውን እና የስራ ሀላፊነታቸውን የሚገልጽ **ደብዳቤ መጻፍ ይኖርበታል፡፡**



# አመሰግናለሁ!